

# 1-3

# ፈቃዱን ማወቅ ይገባል

እርግጥ ነው ብዙ ጊዜ መጸለይ እንደሚገባን አንጸልይም። ኤልያስ “ግደለኝ” ሲል ሙሴ ደግሞ “ስሜን ከመዝገብህ ፋቅ” ብለው ጸለዩ። ሁለቱም ያገኙት መልስ “አይሆንም” የሚል ነበር። ጸሎት ማለት የፈቀድነውንና የጠየቅነውን ሁሉ የምናገኝበት መሣሪያ ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር የጠየቅነውን ሁሉ እንደሚሰጠን ተስፋ አልገባልንም። እርግጥ ነው እንደ በጎ አባት ሆኖ የሚረሳውንና የማይረባውን ጸሎታችንን ካዳመጠ በኋላ ለእርሱ የመሰለውንና ለእኛ ይስማማል የሚለውን ሁሉ ያደርጋል። ጸሎታችን ገና መልስ ያላገኘ መስሎ ከተሰማን፥ ያላየነውና ገና ያልደረስንበት መንፈሳዊ እውነቶችን ሊያመለክተን ይሆናልና በትዕግሥት እንጠብቀው። ሰይጣን ያለንን “ጠይቆ የማግኘት” መብት አግባብ ባልሆነ መንገድ እንድንጠቀምበት ሊያደርግ ይችላልና መጠንቀቅ እንዳለብን አንርሳ። በአገልግሎታችን እግዚአብሔርን በጣም ደስ እንዳሰኘነውና እግዚአብሔር በተራው ደግሞ ይህንን ታላቁን ሥራችንን አይቶ ታላቅ ነገር ለእኛ መክፈል እንዳለበት አድርጎ ያሳየናል። የእግዚአብሔርን ድምጽ ከሰይጣን ድምጽ መለየት ካልቻለን እኛም ይህንን ሃሳብ በመደገፍ ለአይናችንና ለልባችን በጣም ደስ ያለንን ነገር “ጌታ ሆይ፣ ያንን ነገር እፈልጋለሁ፤ ከጠየቅሁህ ደግሞ እንድምትሰጠኝ ቃል ገብተህልኛልና ስጠኝ” በማለት መጸለይ እንጀምራለን። ከፈቃዱ ውጪ የሆነውን ነገር መጠየቅ ብቻ ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር የጊዜ ገደብ እናበጅለትና “ከዚህ ቀን ሳያልፍ እንድትመልስልኝ” እንለዋለን። ከዚህ አልፎ የእምነት እርምጃ የወሰድን መስሎን የራሳችንን ፍላጎት ለማሟላት ከውሳኔ እንደርሳለን። በሌላ በኩል ደግሞ የፈለግነውን ነገር ሳናገኝ የቀርን እንደሆነ በመንፈሳዊ ህይወታችን መዛባት እንጀምራለን። ከዚህ በፊት አምነን የተመላለስንበት መንገድ ሁሉ ልክ እንዳልነበረና እግዚአብሔርን በቅንነት ማገልገል ዋጋቢስ እንደሆነ ይሰማናል። በእምነት የፈለግነውን ሁሉ ለማግኘት እንድንችል በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ይገባናል። ምንም ያህል በክርስትና ሕይወታችን ጌታን የምንወድና የምናፈቅር ብንሆንም ከፈቃዱ ውጪ የሆነው ነገር ምንም ያህል ለእኛ በጎ መስሎ ቢታየንም ሊሰጠን አይችልም። በፈቃዱ ውስጥ የሆነውን ግን ፍጹም እንደማይከለክለን ሐዋርያው ዮሐንስ በመልዕክቱ ያረጋግጥልናል። ***“እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል”*** 1ኛ ዮሐ. 5፥14።

ብዙ ጊዜ ከፈቃዱ ውጪ በሆነው ነገር ላይ ልመናችንን እያቀረብን የጠየቅነውን ባለማግኘታችን ብዙ ተስፋ መቁረጥና መሸነፍ ይደርስብናል። ይህ ሊሆን የሚችለው እምነታችንና ፍላጎታችን በፈቃዱ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በራሳችን ፍላጎትና ምኞት የታጠረ በመሆኑ ነው። ክርስቶስ እርሱ እንኳን የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ ለመፈጸም ይናፍቅ እንደነበረ መረዳት አያዳግተንም። ***“የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው”*** ሲል ይናገራል፤ ዮሐንስ 4፥34። ዳዊትም ***“አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ”*** ይላል፥ መዝሙር 40፥8። ምንም ያህል ትልቅ እምነት ቢኖረን ፈቃዱን ካላወቅን የምንፈልገውን የማናገኝ መሆኑን ስንረዳ በመገረም፥ “በግሌ ለራሴ የሚስማማኝን ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ለምን አስፈላጊ ሆነ?” ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ከሆነ፥ ፈቃዱን ማወቅ እንዴት ይቻላል? ጳውሎስ ***“መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል፤ ራሱ ግን በማንም አይመረመርም። እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን”*** ይላል 1ኛ ቆሮ. 2፥15። ፈቃዱን ማወቅ የተመሠረተው ክርስቶስን በማወቅ ላይ በመሆኑ ምኞታችን ጌታን አጥርተን ለማወቅ ይሁን ***“ስለ በጎፈቃዱ መፈለግንም ማድረግን ም በአንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና”*** ይላል ጳውሎስ በፊሊጲሲዮስ 2፥13 ላይ። ክርስቶስ በዮሐንስ

14፥12-14 *"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፤ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁ፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ"* ይላል። ክርስቶስ "የምትለምኑትን ሁሉ" ሲል ከፈቃዱ ክልል ውጪ የሆነውን ማለቱ እንዳልነበረ መረዳት እንችላለን። እንግዲህ የራሳችንን ፈቃድ መተው ማለት በዕለታዊ ሕይወት ሲታይ ምን ማለት ነው? የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም ማለት፣ የራሳችንን ከእርሱ ራሱ የተቀበልነውን መብት ገለል አድርገን በእግዚአብሔር ፕላን መመራት ማለት ነው። ይኸውም፥ እኛ በፈቃዳችን ልናደርገው የምንችለውን ችላ ብለን የእርሱን ፈቃድ ስንጠብቅ ነው። የእኛን መብት ገለል አድርገን ስንል፥ የትኛውን መብታችንን ነው? መብታችን ስንል፥

1. በአእምሮአችን የማሰብና የማሰላሰ መብት፥
2. ስሜታችንና
3. ፈቃዳችንን ነው

እነዚህ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን መብት ሲሆኑ፥ የእርሱ ፈቃድ በሕይወታችን እንዲፈጸም ስንፈቅድ የራሳችንን ወደ ጎን ገለል እናደርጋለን።

## ለውውይት የሚረዱ ጥያቄዎች

1. ፈቃዳችንን፣ ምኞታችንና አዕምሮአችን በጸሎት ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ሥፍራ አስረዳ።
2. እምነት ለጸሎት ሕይወት ለምን አስፈላጊ የሆነ ይመስልሃል?
3. በሌላ ጊዜ ለሰው ከፍተን ያላሳየነውን ሕይወታችንን አቋም በጸሎት ጊዜ ከፍተን እናቀርባለን ስንል ምን ማለታችን ነው? ከራስህ ሕይወት ጋር ስታስተያየው፤ ጸሎትህ ይህን ያጠቃለለ ይመስልሃል?
4. እግዚአብሔርን በማወቅና ፈቃዱን በማወቅ መካከል ያለውን ግንኙነት አስረዳ።
5. በዚህ በዛሬው ትምህርታችን ያገኘኸው አዲስ ትምህርት ምንድነው? ይህንን ዛሬ ያገኘኸውን አዲስ ትምህርት ወይንም ሃሳብ ቢያንስ ለአንድ ሰው ለማካፈል ሞክር።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**